# ጋሼ መለስ በደንብ በለን?

ባይሞትላትም « ኢትዮጵያ ወይም ሞት!» እያለ ደርጉ የገደለን እኛን ነው እንጂ ኢትዮጵያን አልነበረም። ወያኔው መለስ ግን የገደለን እኛን፣ ከሀገራችን ከኢትዮጵያ ጭምር ነው። በቅድሚያ ኢትዮጵያ ተጠፍጥፋ ከተበጀች መቶ አመቷ ነው ሲል የሀገር ግድያ አዋጁን በዋና ከተማችን አዲስ አበባ ተቀምጦ፣ በገንዘባችን በገዛነው ቴሌቪዥናችን ነገረን። ምን ዓይነት የሱዳን አዚም እንደረጨብን እግዚአብሔር ይወቀው፣ ቁርሱን እንደተከለከለ ህጻን በያለንበት አልጎምጉመን፣ ግፋ ቢልም የተቃውሞ ድምጽና ጽሁፍ አሰምተን «አዎ መቶ ዓመቷ ነው» የማለት ያህል በወረደ ልብ ተስማምተን ዝም አልን። ሪፈረንደም የመረጡትን የእናቱን ሀገር ኤርትራን እናንተ ነፍጠኞች በቅኝ ግዛት በመያዝ የመጀመሪያ ጥቁሮች ናችሁ፣ ስለዚህ የበደላችሁትን ሕዝብ ሽማግሌ አዋቅራችሁ ሂዱና ይቅርታ ጠይቁ ሲለን ምን ዓይነት አፍዝ አደንግዝ እንደቀባን ሳናውቅ የድሮ ወንድሞቻችንን ያለአግባብ ቅኝ ስለገዛናችሁ ይቅርታ አድርጉልን ብለን ትቢያ ልሰን የሀሰት ታሪኩን ጽዋ ተጋትን። ውጭ ሀገር ሆናለች የተባለችው ጣሊያናዊት ኤርትራ ዓይናችን እያየ በኛው ባጤራ ሸምታ፤ ወደእኛው በዶላር ስትሸቅጥና ለዓለም ገበያ አዲሲቱ «የአባጅፋር» ሀገር ሆና ቡና ስትሸጥ እያየን፣ እየሰማን መለስ ነፍጠኞችና ትምክህተኞች ጉርብትናችንን አይወዱትም ሲል በተቀማነው ላይ ስድቡን ሲጨምር ይሁና ብለን ዝም አልን። ይህም ሲያንስ ነው ይበለን!!

ዱዲ ሀብት የሌላት ላርቫ ሀገር ኤርትራ አቶ መለስ ከፍተው በሰጡት የቤታችን ሀብት ደርጅታና መሳሪያ ሸምታ አፍንጫችንን ስትለን፣ 70 ሺህ ወጣት ለሽፍቶቹ እሳት ማገዶነት አቅርበን ወይ ከባድሜአችን ወይም ካለቀው ትውልዳችን ሳንሆን ለሌላ ዙር እልቂት ሲንጎማለሉ እያየን ምን ዓይነት ክታብ እንዳስተበተቡብን ሳናውቅ እያየን እንቅልፍ፣ እየሰማን ድንዛዜ ይዞናል። ይህም ሲያንስ ነው ይበለን!

አልበሽርን ጠርተው እንካ የድርሻህን፣ ካነሰህ ደግሞ ይጨመርልሃል እያሉ የሀገር ሙክት ጥለው ቅርጫ ሲያድሉ፤ ሳልቫ ኪርና ምዋይ ኪባኪም ለእኛም ይሰጠን በሉ! ብለን በሀገራችን ላይ ተሳልቀን ሀገር ለገደሉት መለስ፣ የፌዝ ድጋፍ ሰጥተን ይኼው በዝምታ ሰምጠን ተኝተናል። አረ ይበለን ይህም ሲያንሰን ነው!

ኑሮው ጣራ ሆኖ፤ ጣር ሲያስምጠን፣ በዋጋ ምሰሶ ላይ ሲሰቅሉንና ሲያወርዱን እየተብሰለሰልንና እህህ እያልን የቁም ሞታችንን ለምደነው ዝም ማለታችን እውነት ቢቀሰቅሱን ነፍስያችን በውስጣችን ይኖር ይሆን? እንኳን እኛ ራሳችንን ቀርቶ አቶ መለስም ቢሆኑ«ኑሮ ካሉት የመቃብር ይሞቃል» ዝምታችን ሳይገርማቸውና ሳይደንቃቸው አይቀርም! አረ ይበለን ይሄም ሲያንሰን ነው!

ትግራዩን « እቲ አምሃራይ ክበለኹካ ኢዩ»! ለኦሮሞው ነፍጠኛ ሊመለስ ነው! ኦሮሞ ማለት ኦነግ ነው! ለወላይታ የአኩስም ሐውልት ምኑ ነው! መንገዱን ጨርቅ ይድርግላችሁ! ደደብና ጨምላቃ.....! እያለ ሲፈረካክሰንና አዋርዶ ሲያረካክሰን፣ እንዲህ እኮ አለ! እንዲያ ተናገረ! ብለን ጉዳዩ የማንነትና የሀገር ህልውና እስከማይመስለን ድረስ ተጠላልፈን ዝምታ መምረጣችን ምን ብንሆን ይሆን?

ሌባ ቱጃሮችን እንደእንጉዳይ በየጓሮአችን አፍልቶ፣ ሰራተኞችን ቀምቶ ባዶ እጃቸውን ሲሰድና ተግጦ ካለቀው ሥጋችን ላይ የፈቀፈቀውን ሀብታችንን ቢሊዮኖች ዶላር ሲያሻግር እየሰማን ዜና ከመስራትና ዲስኩር ከማሞቅ ባለፈ ወዲያውኑ ረስተን ለሌላ መጪ ዱላ እራሳችንን ማዘጋጀት እውን ይህ የጤና ነው? እ ረ ይበለን ይህም

ሲያንሰን ነው!

ሀገር ጥሎ መሰደድ የሀገር ባህል ዘፈን መስሎ፣ በአራቱም ማእዘን በ«እየየው፣ እየየው»ቁዘማ ስንኮበልል፣ ለባህር አሳ እራትና ለኩላሊት ንግድ አካላችን ሱቅ በገላዬ ሆኖ መቅረቱን ከማርጎምጎም ባላለፈ አሜን ብለን፣ እንደእጣ ፈንታችን ቆጥረን መቀበላችን እውን የሺናሻ ቅጠል ጨቅጭቀው አልረጩብንም ይሆን? ኧረ ይበለን ይህም ሲያንሰን ነው!

ሴቶቻችን ስደቱንና አካል እንደሸቀተ ከመሸጣቸው አልፎ ጉልበታቸውን በኪሳራ እየገበሩ፣ አልፎ ተርፎም በፈላ ውሃ ሲገነትሩ እያየን፣ ተፎቅ ተወርውረው መሽመድመዳቸውን እየሰማን፣ ኢትዮጵያዊ ያልገባበት የዓለም ጫፍ ካለመኖሩም በላይ የድረሱልኝ ጩኸቱን የሚሰማለት አድማጭ መጥፋቱን እያስተዋልን ያለነው ዝም ብለናል።

«ጠመንጃ እራሱ ገድሎ፣ እራሱ ይጮሃል» እንዲሉ እኛው በመለስ የሽብር ድርጊት የምንደርስበት መላ ጠፍቶንና ባርነቱን አሜን ብለን መቀበላችን አንሶት፣ ሥልጣኔን ትመኛላችሁ አሉ! በሚል ዓይነት ስላቅ አሸበራችሁኝ ብሎ ከሱቅ ከረሜላ ገዝቶ እንደሚመለስ ህጻን ያህል መናኛ ጊዜ አድርጎ በመቁጠር 20 እና እድሜ ልክ ፈረድኩባችሁ ሲለን ይሄ ሰው ቁጥር አያውቅም እንዴ? ብለን ቀልደን ዝም ስንል ኧረ ይበለን ይሄም ሲያንሰን ነው!

ፈረንጅ አያድናችሁ፣ አና ጎሜዝ አታስጥላችሁ! ብሎ በተለመደው ሀለዋ ወያኔ ተከርቸም ሲወረውር፣ ግንባር ግንባሩን ነድሎ፣ ባንክ ሲዘርፉ አገኘሁ ብሎ ዜና ሲሰራ ሁሉን አይተን ሰምተን ዝም አልን!

ሰው ሲያፍን፣ ሬዲዮ ሲያፍን፣ ቴሌቪዥን ሲያፍን፣ የምርጫ ድምጽ ሲያፍን፣ ጉባዔ ሲያፍን፣ ስደተኛ ሲያፍን፣ ሁሉን ሲያፍን ላጠረው ትንፋሻችን ቁና ቁና ከመተንፈስ ባሻገር ዝም ማለታችን እውነት የጤንነት ይሆን?

አንድ እንዳንሆን ሌት ከቀን ሲሰራ እኛው ፈቃደኝነታችንን ሰጥተን፣ ከባርነት ላንወጣ፣ ላናወጣ፣ እኔ የኦሮሞው ነኝ፣ እኔ ደግሞ የሶማሌ ነኝ፣ እኔ ደግሞ የጋምቤላ፣ እኔ ደግሞ የትግራዩ፣ እኔ ደግሞ የአርበኛው ወዘተ መቶ ብጥስጥስ ሆነን ብጥስጥሱና ብትንትኑ በወጣ ሕዝብ ላይ ነጻ አውጪ ሆነን፣ ተግጣ፣ ተጠርባ አጥንቷ በወጣ ሀገር ላይ «አባከና» የሚለው ቆጣሪ እንደሌለው ውሻ ስንናጭ መለስ ዛሬም ድረስ አንድ መሆን አይችሉም ብሎ በማመን «መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ» እያለንና መንገዱን ጨርቅ ማድረግ ስንጀምር «ዓለም አቀፍ አሸባሪ» እያለ አጥር ሲያበጅብን እውነት ምን ሆነን ይሆን? ኧረ ይበለን ይሄም ሲያንሰን ነው!

እንዴት አድርጎ እንደናቀን ይገባን ይሆን? እንዴትስ አድርጎ እንዳዋረደን ተሰምቶን ይሆን? እንዴትስ አድርጎ እንዳለያየን፣ እንዴትስ አድርጎ አይጥና ድመት እንድንመስል እንደሰራልን ገብቶን ይሆን? ውርደቱን ብርድ አድርገን ተከናንበን በፍርሃት ዝም ስንል የሞቀን ስለመሰለው ገና ምርጥ ምርጡን ውርደት ይደርብልናል!

ሀገር ስትሞት እያየን ታሪክ ነበረን፣ አኩስምና ላሊበላ፣ ጀጎልና ሶፍ ዑመር ማለቱ ለየትኛዋ ኢትዮጵያ ይሆን? መለስ ጨካኝና ጎሊና ቢስ መሆኑ አልገባን ይሆን?

መለስ ኢትዮጵያን ረግጦ ካልገዛ ብትንትኗ ቢወጣ ግድ የሌለው የአያቶቹ ልጅ መሆኑን አንገነዘብ ይሆን? ካልገባን እንግዲያውስ ይበለን ሲያንሰን ነው!

አላነሰንም፣ ይልቁንም በዝቶብናል፣ መሮናል፣ ሰልችቶናል፣ አንገፍግፎናል፣ ከርፍቶናል፣ ውርደት ከብዶናል፣

ሀገር ናፍቆናል፣ የመብት መረገጥ ሰልችቶናል የምንል ከሆነ፣ መለስ 20 ዓመት አላረፈምና ከረፈደም በኋላ ቢሆን እንኳን አንድ ከሆንን አንድ ዓመት አይፈጅብንም ካሰብንበት እንደርሳለን! እንደርስበታለን!
እባካችሁ ወደድንም ጠላንም ሁላችን መከራው ደርሶብናል፣ የአንድ ሀገር ሕዝቦች ነን አንድ እንሁን! ቋንቋችን ቢለያይ ቆዳችን አንድ ነው! ደማችን አንድ ነው! ወንዛችን አንድ ነው! ለየብቻ የምንጎትተው ገመድ እኛኑ አስሮ ከሚያስቀረን በቀር የመለስን ሴራና ክፋት ማሰር አልቻለም፣አይችልምም!
መለስ ያዞረብን መተትና ድግምት ልዩነታችንን ነው። የሺናሻ ቅጠል ወይም የሱዳንም አስማት አይደለም። ፈሪዎች ናቸው፣ ሱሪ የላቸውም ብሎ ንቆን ነው። «መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ» እያለ ሁል ጊዜ በቴሌቪዥኑ ሳይቀር የሚያሰማው ትምክህት ምን እንደሆነ አወቃችሁ? ፈሪዎችና ቡከኖች ስለሆኑ ቂጣቸውን ከማወዛወዝና ቦርጫቸውን ከመዳበስ ባለፈ ሽብ፣ሽንቀጥ ብለው በመታጠቅ ለእኔ ስጋት አይሆኑም ብሎ መቶ በመቶ በመደምደሙ የተነሳ ነው። 20 ዓመት ተበታትነን ያለቀስነውን ያህል አንድ ላይ ሆነን አንድ ዓመት አልቅሰን ቢሆን እግዚአብሔርም ይሰማን ነበር፣ የቆራጥነት እምባችንም መለስን አስማት ሆኖ ያጠፋው ነበር። አሁንም አልረፈደም፣ እንደርሳለን፣አንድ እንሁን፣ በገንዘብ፣ በሃሳብ፣ በትጥቅ፤ በፖለቲካው፣ በጎቡእና በገሃድ፣ በሀገር ውስጥና በውጪው፣ በዘመድና በአዝማድ ትግሉን እናቀጣጥል! ከ 20 ዓመት መከራ የአንድ ዓመት ትግል ይሻላል። መለስ የእውር ድንብሩን የሚወስደው እያንዳንዱ እርምጃና የኑሮ ጫና የትግሉን አካል ያበዛዋል፤ ከተወሰነ አቅጣጫ ሳይሆን እሳቱን ዙሪያ ገብ ያደርገዋል። ኃይል አሰላለፉ በጠመንጃ ከታመኑት ጥቂቶች በቀር ጠመንጃ የያዘውን ጨምሮ ወደ ብዙኀኑ ያደርገዋል። ጠመንጃ የታጠቀው የመለስ ታማኞችን ጨምሮ ከነመለስ ጋር አብረው አጥፍተው ለመጥፋት የሚፈልጉ አድርጎ የሚያስብ ካለ እሱ ሞኝ ነው። ጉዳዩ የእኛ አንድነትና ብርታት እንጂ በ 11ኛው ሰዓት ሁሉም ከሀገርና ከሕዝብ ጎን እንደሚሆን አይጠረጠርም። በአጠቃላይ አንድ እንሁን! አንድ ላይ እንስመር! እንተባበር! እስኪ ሁላችንም መከራ ይሰልቸን! ከወሬ ባለፈ በተግባር የሚያሰራ መንፈስ ይውረድብን!
አለበለዚያ!....አለበለዚያማ! አልበዛብንም ጋሼ መለስ ሲያንሰን ነው፣ በደንብ በለን እንበለው!!
እኔስ አልለውም! ስንት ዘመን ልኖር ነው? እንደኢትዮጵያዊ ኮርቼ ሳልኖር ከመሞት እንደኢትዮጵያዊ አስቤ ለመኖር ወስኛለሁ! አንተስ? አንቺስ? ጋሼ መለስ በደንብ በለን?

(ሊላይ ከጀርመን)